"MO-ANBESSA"

THE CONQUERING LION

የሞዓ አንበሳ መተዳደሪያ ደንብ

ሞዓ አንበሳ

በኢትዮጵያ የዘውድን ህልውና ዕውን ለማድረግ የተቋቋመ ጊዜያዊ አሰባሳቢ አካል።

ስም፣ ሞዓ አንበሳ።

ዓላማ፣

ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት እጅግ አስከፊና አስጊ የሽግግር ጊዜ ውስጥ ያለን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድና ሲያያዝ የመጣውን የአባቶቻችንን ባህልና ቅርስ እንደነበረና እንደተጠበቀ አድርጉ ለማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ባለን ከፍተኛ ምኞት ተነሳስተን ሞዓ አንበሳ ተብሎ የተሰየመውን አሰባሳቢ አካል አቋቁመናል።

የድርጅቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ባላት ታሪክ፣ ባህል ወግና ሥርዓት መሠረት ያገሪቱ ነፃነት፣ የሕዝቡ አንድነት፣ ዕኩልነት ተጠብቆ የኖረው በዘውዱ የበላይ ሰብሳቢነት መሆኑን በማረጋገጥ ነው። ሕዝቡ ከባህሉ፣ ከልማዱና ከሃይማኖቱ ጋር ዘውዱ የተሳሰረ በመሆኑ በዚሁ መኖርና መተዳደር መፈለጉን ሕዝቡ ራሱ የመጀመሪያው ምርጫው ሆኖ በመታየቱና በመፈለጉ ይህንኑ ሕዝባዊና ብሔራዊ አደራና ፍላጐት ፍፁም ለማድረግ የተቋቋመ ነው።

እንደሚታወቀው ዘውድ የሕዝብ ነው። አገር የሚረጋጋውና የሕዝብ ሰላም የሚሠፍነው በዘውድ ነው። ለአምስት ሺህ ዘመናት ፀንቶ የቆየውም በዚህ ምክንያት ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዘውድ የተዳከመበትና ከቦታ ቦታ የተሰደደበትም ወቅት ነበር። ዘመነ መሣፍንት ተጠቃሽ ማስረጃ ሲሆን ይህም በኢጣሊያና በአሁኑ በኮሙኒስቶች ወረራ ወቅትም ተደግሟል። ይህም ሲሆን ዘውድ ጠፋ፣ ተደመሰሰ ማለት አይደለም። ችግር ላይ የነበረባቸውን ወቅቶች ለማሳየት ያህል ነው እንጂ!!

የሕዝቡና የአገሪቱ ልዩ መታወቂያ የሆነው ዘውድ በተመልካቾች ዘንድ የጌጥ፣ የመከበሪያ፣ የመመኪያና የአንድነት ዓምድ ሆኖ ይታወቃል። ስለዚህም ዘውድ የሕዝቡ መሠረት፣ የሕዝቡ ዋልታ፣ የታሪኩ ጋሻ ነው። ስለሆነም ይኸው ይዘትና ሂደት እንዲቀጥል ለማድረግ ሞዓ አንበሳን በአስተባባሪ አካልነት ማቋቋም አስፈለገ።

የበላይ ጠባቂ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ አምኃ ሥላሴ ናቸው።

የሥራ አስኪያጅ ቡድን አባላት

1) የሰብሳቢው አካል ሊቀ መንበር
2) የሰብሳቢው አካል ም/ሊቀ መንበር
3) የሰብሳቢው አካል ዋና ጸሐፊ
4) የሰብሳቢው አካል ም/ ዋና ጸሐፊ
5) የሰብሳቢው አካል ገንዘብ ያዥ

እንደአስፈላጊነቱ የሥራ አስኪያጅ ቡድን የተለያዩ ክፍሎችን ይመሠርታል።

አባልነት

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ የሞዓ አንበሳን ዓላማ የሚደግፍ ሁሉ አባል መሆን ይችላል። እንዲሁም ዘውድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የበላይ ስለሆነና ሁሉንም ስለሚያቅፍ ከሞዓ አንበሳ ጋር አብሮ ለመሥራት ይችላሉ።

ተግባር፣

የሞዓ አንበሳ ተግባር በማንኛውም አመቺና ተስማሚ በሆነ መንገድ ሁሉ የሕዝብ ቅስቀሳ እያደረገ የዘውድን አቋም እንዲደግፍ የሚረዱትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል። ከነዚሁም መካከል፣

1) ዓላማውን የሚደግፉ ጽሑፎችንና ዜናዎችን ማሠራጨት
2) የሕዝብ ዕርዳታ አውታሮችን መዘርጋት
3) ሥራ አስፈፃሚ ቅርንጫፎችን በያሉበት ማቋቋም
4) አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ የአባላት ምዝገባ ማከናወን። ወዘተ ...

የሞዓ አንበሳ የሥራ ፍፃሜ

ሞዓ አንበሳ በኢትዮጵያ በሕግ የተወሰነ የዘውድ መንግሥት መልሶ ካቋቋመ በኋላ የተግባሩ ፍፃሜ ይሆናል። ይህም የሕዝቡ ሙሉ የዲሞክራሲ መብት የተከበረበት በሕግ የተወሰነ የዘውድ መንግሥት እንደ እንግሊዝና እንደ ጃፓን ዓይነት ነው። በውስጡ ግን ብዙ ፓርቲዎች የሚኖሩበትና በሕዝብ ምርጫ አገሪቱን የሚያስተዳድሩ አካላት የሚገኙበት ይሆናል።